**የአውሮፓ ሕብረት**
**የኢትዮጵያ የምርጫ ዛቢ ልዑክ 2002**
የህዝብ ተወካዮች ም/ቤትና የክልል ም/ቤት ተወካዮች ምርጫ


**በአስቸኳይ የሚለቀቅ**

## ጋዜጣዊ መግለጫ

**አዲስ አበባ፣ ሚያዚያ 15 ቀን 2002 ዓ.ም**

90 የሚሆኑ የረጅም ጊዜ የአውሮፓ ሕብረት ታዛቢዎችን የያዘ ቡድን ቅዳሜ ሚያዚያ 16 ቀን 2002 ዓ.ም ኢትዮጵያ ይገባል። ታዛቢዎች ስለተለያዩ የምርጫው ጉዳዮች ተከታታይ ገለጻዎችን ለማዳመጥ ለ3 ቀን አዲስ አበባ ከቆዩ በኋላ ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ይሠማራሉ።

የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች ከምርጫ ቀን በፊት ከሚሠሯቸው ድርጊቶች መካከል የአካባቢውን የምርጫ ባለስልጣናትን፣ ተወዳዳሪዎችን ፣ የፓርቲ ተወካዮችን፣ የሲቪል ማሕረሰብ ድርጅቶችንና ድምጽ ሰጪዎችን ማግኘትን ያካትታል። በተጨማሪም ምርጫውን፣ አቤቱታዎችን፣ ቅሬታዎችን እንዲሁም የምርጫውን ዝግጅቶች ይከታተላሉ። በምርጫው ዕለት (ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም) ከምርጫ ጣቢያዎች አከፋፈት ጀምሮ እስከ ድምጽ መስጠት፣ መዝጊያና ቆጠራ ያሉትን ሁሉንም የምርጫ ደረጃዎች ይታዘባሉ። ግኝቶቻቸው የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ልዑክ የሚያደርገው አጠቃላይ ግምገማና ምዘና አካል ይሆናሉ።

የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች ቡድን ከምርጫው ዕለት አንድ ሣምንት ቀድመው ይገባሉ ተብለው በሚጠበቁት የኣጭር ጊዜ ታዛቢዎች ይጠናከራል። ሁለቱም የረጅም እና የአጭር ጊዜ ታዛቢዎች በጣቢያና በፌደራል ደረጃ የውጤቱን የቆጠራ ሂደትና የውጤት እወጃውን ይታዘባሉ። የታዛቢ ቡድኑ የመስክ ጉዞውን ቀንና ሰዐት በተመለከተ ለመገናኛ ብዙሀን ወደፊት መግለጫ ይሰጣል።


የታዛቢ ቡድኑ የመስክ ጉዞውን ቀንና ሰዓት በተመለከተ ለመገናኛ ቡዙሃን ወደፊት ምግለጫ ይሠጣል።



**ለሚዲያ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ስማቸው የተጠቀሰውን ያነጋግሩ።**
አፕስ ዶካ - ፕሬስ ኦፊሰር
ስልክ: +251(0)920537623
E-mail: agnes.doka@eueom-ethiopia.org